# ለአስረኛው የአባይ ወንዝ ድልድይ አስር ምክንያቶች

# 10 reasons for 1oth Abay river crossing bridge

## 1 መግቢያ

ከኢትዮጲያ የስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሰረት ታላቁ የአባይ ወንዝ 1450 ኪሎሜትር አጠቃላይ ርዝመት ያለው ሲሆን 800 ኪሜ ያህሉን ርቀት በሀገር ውስጥ የሚጓዝ ነው፡፡ ከደቡባዊ የጣና ሀይቅ በመነሳት የሀገሪቱን ሰሜን ምእራብ እየተጠማዘዘ ወደሱዳን የሚገባው አባይ 400 ኪሜ ያህሉን በጥልቅ ሸለቆ ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ወንዙን ለመሻገር እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ከቀሪው ግማሽ የሀገሪቱ ክፍል ጋር ያለድልድይ ለመገናኘት አመቺ አይደለም፡፡

ይህ ታላቅ ወንዝ ከመነሻው ከጣና 40 ኪሜ ያህል ወረድ ብሎ 45 ሜትር ከፍታ ላይ ወደ ታች ሲወርድ የሚያሳየው የተፈጥሮ ውበት ጢስ አባይ የሚል ስያሜን አግኝቷል፡፡ ምንም እንኳ ወደ ጣና ሀይቅ የሚገቡ ገባር ፍሳሾች ቢኖሩም ግሼ አባይ ተብላ የምትታወቅ አንዲት አነስተኛ ምንጭ የአባይ መነሻ እንደሆነች ይታመናል፡፡ ይህ ወራጅ ተፋሰስ ያድግና ወንዝ ሆኖ ትንሹ አባይ ወይም ግልገል አባይ በሚል የሚታወቅ ሲሆን ከመራዊ በሰሜን አቅጣጫ ወደ ጣና ሀይቅ ይቀላቀላል፡፡

በጎንደር ግዛት ጎርጎራ ከሚባለው ጀምሮ ማጌች፣ ሰሜንና ደቡብ ጉመራ፣ ርብና ቁልጤ የሚባሉ ትናንሽ ወንዞች የጣና ሀይቅን የሚቀላቀሉ ሲሆን ከሀይቁ ወጥቶ የአባይ ወንዝ ከባህርዳር ከተማ ጀምሮ እስከሜዲቴራንያን ባህር የሚያዘልቀውን ረጅሙን ጉዞ ይቀጥላል፡፡ በጉዞው ላይ የአባይን ወንዝ መጠን እየጨመሩና እያበዙ የሚሄዱ በርካታ ገባር ወንዞች ያሉ ሲሆን እነዚህንም ለመጥቀስ ያህል ወንቃ፣ በሽሎ፣ ዋለቃ፣ ዋንጪት፣ ጀማ፣ ሙገር፣ ጉደር፣ አግወል፣ ነዲ፣ ዲዴሳ፣ ዳቡስ፣ ሀንዳሳ፣ ቁል፣ አባያ፣ ሳዴ፣ ታሚ፣ ጫ፣ ሽታ፣ ሱሀ፣ ሙጋ፣ ጉላ፣ ተምጫ፣ ባጫት፣ ካትላን፣ ጂባ፣ ጨሞጋ፣ ወተርና በለስ ይጠቀሳሉ፡፡

የአባይ ወንዝ "ጥቁር አባይ" ወይም "ብሉ ናይል" እየተባለ ቆይቶ የኢትዮጲያን ግዛት ተሻግሮ ወደ ሱዳን በመግባት ካርቱም ከተማ ላይ ነጭ አባይ ከሚባለው አጋሩ ጋር እንደተቀላቀለ ናይል በሚል መጠሪያ ወደዘላቂ ቤቱ ወደሜዲቴራንያን ባህር ይገባል፡፡ እንግዲህ አባይ ወንዝ በትውልድ ሀገሩ በኢትዮጲያ 800 ኪሜ ያህል ሲጓዝ ከ17ኛው ክፍለዘመን አንስቶ እስከ 2000 ሚሊንየም ድረስ 8 ያህል ልዩ ልዩ አይነት ድልድዮች የተገነቡለት ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ተጨማሪ ሁለት ድልድዮች እንዲገነቡ ተወስኖ 9ኛው ድልድይ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን 10ኛው ድልድይ ደግሞ እነሆ በውቢቱ የባህርዳር ከተማ ላይ ሊገነባ በመባቻው ላይ እንገኛለን፡፡

አባይ ወንዝን ለመሻገር ድልድይ የመገንባቱ ሂደት በየዘመኑ እጅግ ብዙ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ውጣ ውረዶችን የሚያስተናግድና ከባድ ውሳኔን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን የመንገዶቹና የድልድዮቹ መገንባት ለሀገር የሚሰጡት ጠቀሜታ ታላቅ በመሆኑ የቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው መገንባታቸውና እየተገነቡ መሆኑን ከቀድሞውና ከአሁኑ ታሪካችን እንረዳለን፡፡

የአባይ ወንዝ ድልድዮች ግንባታ ጅማሬ የ 400 አመት የጉዞ ታሪክ ያላቸው ሲሆኑ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አሁን ሊጀመር የተዘጋጀው 10ኛው የአባይ ወንዝ ድልድይ ከመጀመሪያው ድልድይ በትክክል 400ኛ አመቱን ( 1618- 2019) ጠብቆ የሚገነባ መሆኑ ድንቅ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው፡፡

ሌላኛው አጋጣሚ የዛሬ አራት መቶ አመት የመጀመሪያው ዘመናዊ ድልድይ ሲሰራ በዘመኑ በአውሮፓ የነበረውን የግንብ ድንጋይ አርች ዲዛይን ተከትሎ የተሰራ ሲሆን ዛሬም ላይ የሚገነባው ድልድይ ከሁለት አስርት አመታት ጀምሮ የወንዞችን ስፋት በሚመጥን መልኩ ዘመናዊ ድልድይ ተብለው በአውሮፓ ፈረንሳይ ሀገር ተፈልስፎ በጃፓንና በእስያ ሀገራት እየተዘወተረ የመጣ ኤክስትራዶስድ የተባለ የድልድይ አይነት እየተገነባ መሆኑ ነው፡፡

ይህ አስረኛው የአባይ ድልድይ 380 ሜትር ርዝመት እንደሚኖረው ዲዛይኑ የሚያመለክት ሲሆን ሲጠናቀቅ በሀገራችን በርዝመቱ ሁለተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህም በድልድይ አይነቱም ሆነ በርዝመቱ በሀገራችን ሁለተኛ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት በአይነቱ ተመሳሳይ የሆነውና በአባይ ሸለቆ የተገነባውን ባለ 303 ሜትር ድልድይ የመጀመሪያው ድልድይ ተከትሎ ሁለተኛ ሲሆን በርዝመቱ ደግሞ አሁን የተከዜ ወንዝን አቋርጦ የሚያልፈው 440 ሜትር ርዝመት ያለውን ድልድይ ተከትሎ ሁለተኛ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይሁንና ግን እስካሁን በሀገራችን ካለው የድልድይ ግንባታ ልምድ በመነሳት ከዋጋ አንፃር ከ 250 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉ ያልተሰማ ሲሆን ይህ ድልድይ ግን እስከ አንድ ተኩል ቢሊየን ብር ድረስ የዋጋ ግምት መያዙ ከተሰማበት ቀን አንስቶ ኮንትራቱም ሊፈረም እስከተቃረበበት ወቅት በአንዳንዶች ዘንድ ለአንድ ድልድይ ይህን ያህል ዋጋ ማውጣት ተገቢ ነውን? የሚል ጥያቄ ለንግግርና ለክርክር መቅረቡ ምስጢር አይደለም፡፡

በእርግጥ ከብዙ አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ መለኪያዎች አንፃር ይህ ጥያቄ ለምን ተነሳ ማለት አይቻልምና እንደው ጥሩ ድልድይ ከመፈለግ ደረቅ ምኞት ባለፈ ግን ብዙዎችን ሊያሳምንና ሊያስማማ የሚችል ምክንያቶችን ማቅረብ ሙያው የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ ቀድሞውንም የጃፓን መንግስት በትብብር ድልድዩን እንዲሰራልን ብዙ ውይይቶች፣ የሳይት መረጣና የቴክኒክ ቡድንን ባህርዳር በማመላለስ በማሳመኛነት ከቀረቡ አንኳር ነጥባች መካከል ጥቂቶቹን በመውሰድና የበለጠም ግልፅና ጠንካራ በማድረግ *"ለአስረኛው የአባይ ድልድይ አስር ምክንያቶች"* በሚል ርእስ የሚከተሉት ነጥቦች ተዘጋጅተው በመቅረባቸው የብዙዎችን ቀልብ ሊስብ ችሏል፡፡

በዚህም ምክንያት የሆነ ተለዋጭ አዲስ ድልድይ መገንባት ከሚለው ፍላጎት በላይ በእርግጥም ዘመናዊ ድልድይ እንደሚያስፈልግ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ዘንድ ሁሉ ተቀባይነት በማግኘቱ የዋጋው ውድነት በሁለተኛ ደረጃ እንዲታይና ይልቁን ግንባታው በተቻለ ፍጥነት እንዲጀምር ጉጉት የሚጭር ሆኖ ተገኘ፡፡ በዚህም ውሳኔ መሰረት የሁሉ አይኖች በጅማሬው ላይ ሆነና ቀጣይ ትኩረት የኮንትራት ውል ማሰርና የመሰረት ድንጋይ ወደማኖር ለግንባታው ሂደትና ለፍፃሜው ደግሞ ርብርብ ለማድረግ ቃል ወደ መግባት ሆነ፡፡

ይህ ውሳኔ ከማንም በላይ የድልድዩ አይነት ምን ይሁን በሚለው የመረጣ ሂደት ጉዳይ ከ አስር አመታት በፊት ጀምሮ ሲወጥኑና ልዩ ልዩ የፋይናንስ ማፈላለግና የፕሮጀክት አፈፃፀም አማራጭ መንገዶችን ሲያጠኑ ለነበሩ የኢመባ የድልድይ መሀንዲሶች፣ ውቢቷ ባህር ዳር አማራጭ አዲስ ድልድይ እንዲኖራት ለረጅም አመታት ደፋ ቀና ሲሉ ለነበሩ የከተማዋ አስተዳዳሪዎች፣ በተለያየ አጋጣሚ በፕሮጀክቱ ዙሪያ ምክረ ሀሳብ ሲያቀርቡ ለነበሩ ባለሙያዎች፣ በፕሮጀክቱ ዲዛይንና ግንባታ ለሚሳተፉ ባለሙያዎችና የፕሮጀክቱን ቀረፃ አስተዳደርናና ትግበራ ሙሉ ሀላፊነት የተሸከመው አሰሪ መስሪያ ቤት ኢመባ ጭምር እንዲሁም ለመላው የኢትዮጲያ ህዝብ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

## 2 አስሩ ምክንያቶች

ይህ አዲሱ 10ኛው የአባይ ወንዝ ድልድይ አሁን ዲዛይን በተደረገው መሰረት ተወጣሪ combination of Cable Stayed and Box Girder ( Extradosed) ዘመናዊ ድልድይ ሆኖ እንዲሰራ ያስፈለገበትን ምክንያት ከሚገልፁት የምህንድስናና የቴክኒክ ጥናቶች ዝርዝር በተጨማሪ በተያያዥነት የቀረቡት አስሩ መሰረታዊ ምክንያቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

- ይህ አዲስ ድልድይ በአሁኑ ወቅት ዋጋው ውድ ቢመስልም የሀገር ሀብትንና እሴትን ማሳደግ አስፈላጊ ነው የሚለውን አለም አቀፋዊ አስተሳሰብን በመቀበል የሀገር ቋሚ ቅርስ ሀብትና ኩራት ከመሆን አልፎ ቀጣዩ ትውልድም የተሻለና የበለጠ ነገር እንዲሰራ ለማነሳሳትና በሀገራችን የድልድይ ምህንድስና ደረጃንም ለማሳየት ጭምር ዘመናዊ ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- ከመንገድ ደረጃና ስፋት አንፃር እንዲሁም በሀገራችን እየጨመረ ከመጣው የትራፊክ ፍሰት ብዛትና አይነት አንፃር የሱዳንን ፖርት በመተማ በኩል ከመሀል ሀገር ጋር በማገናኘት ከጅቡቲ መንገድ ቀጥሎ ሁለተኛው የንግድ ወጪና ገቢ ኮሪደር በመሆኑ ደረጃውን የጠበቀ መንገድ ሊመጥን የሚችል ረጅምና ሰፊ ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- ይህ ዋና መንገድ ( አውራ ጎዳና) በሀገራችን ካሉት ዋና መንገዶች አንዱ ሲሆን ከዋና ከተማችን ከአዲስ አበባ ተነስቶ ደብረማርቆስ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ሽሬ፣ አክሱም ድረስ በመዝለቅ ከአንድ ሺህ ኪሜ በላይ በሆነ ርዝመት መሀል ሀገርን ከሰሜን ጋር በማገናኘት ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ ዘመናዊ ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- ከኢትዮጲያም አልፈንም አፍሪካን በመንገድ ለማገናኘት ከ50 አመታት በላይ በአፍሪካ ህብረት ፅ ቤት በኩል እየተደረገ ያለው ጥረት አካል የሆነው ከኢንተር አፍሪካ መንገዶች አንዱና ከግብፅ ካይሮ እስከ ደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ድረስ በመዘርጋት ላይ የሚገኘው ዋና መንገድ አካል በመሆኑ በዚህ አፍሪካአቀፍ ባህርይ ባለው መንገድ ላይ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅምን ለኢትዮጲያ ለማስገኘት ዘመኑን የሚመጥን ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- ይህ ድልድይ የሚገነባበት ወንዝ ብሉናይል ተብሎ በአለም የሚታወቅና በርዝመቱ በአለም የአንደኝነትን ስፍራ የያዘው የናይል ወንዝ አካል በመሆኑ እንዲሁም የናይል ወንዝ በሚያልፍባቸው እንደ ዩጋንዳ ሱዳንና ግብፅ ሀገሮች የተገነቡት ድልድዮች እጅግ ዘመናዊና አይንን የሚስቡ በመሆናቸው እኛም የሀገራችንን ደረጃ ከመጠበቅ አንፃር በዚህ ስፍራ ዘመናዊ ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- የባህርዳር ከተማ በአፍሪካ ትልቁ በሆነው የጣና ሀይቅ ዳርቻ የምትገኝ በመሆኗ ከዚህ እውቅ ሀይቅ አፍ ላይ ይህን መሰሉ ዘመናዊ ድልድይ መገንባት የከተማዋ መለያ ምልክት ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ዘመናዊ ድልድይ መገንባት ተገቢ ነው፡፡
- በብዙ ሀገራት የከተሞችን ውበት ከሚጨምሩ መሰረተ ልማቶች አንዱ ከተሞችን ለሁለት ከፍለው የሚሄዱ የወንዝ ተፋሰሶች በዋናነት ይጠቀሳሉ ፡፡ በሀገራችን በኢትዮጲያ ባሉ ከተሞች ይህን አይነት ተፈጥሮ ብዙም ባይኖረንና ወደፊት ግን አቅማችን እንደፈቀደ ሰው ሰራሽ ተፋሰሶችን ልንሰራ ብንችልም በተፈጥሮ ፀጋ የተሰጠንን ደግሞ በአግባቡ መጠቀም የሁላችንም ሀላፊነት ነውና በዚህ ረገድ ይህ አባይ ወንዝ ከጣና አፍ ገና ሲወጣ በመስፋፋት ላይ ያለችውን የባህርዳር ከተማ ለሁለት ከፍሎ የሚያልፍ በመሆኑ ብዙ ህዝብ በሚኖርበት ከተማ መሀል ለመሀል በሚያልፍ ወንዝ ላይ ዘመናዊ ድልድይን መገንባት የከተማዋን ውበትና ኩራት ከመጨመሩም በላይ ይህን ተከትሎ የሚመጡ የመሰረተ ልማት አውታሮች ለከተማዋ ከፍተኛ ገቢ እንደሚያመነጩ ስለሚታሰብ ዘመናዊ ድልድይ መገንባቱ ተገቢ ነው፡፡
- ባህርዳር ከራሷ አልፋ ወደፋሲል ቤተመንግስት፣ ወደ ዳሸን ተራራ፣ ወደላሊበላና ወደ ጥንታዊ የስልጣኔ ከተማ አክሱም የሚሄዱ የሀገርውስጥና የውጭ ጎብኝዎችን የምታስተናግድ በመሆኗ በዚህ መንገድ የሚያልፉ ሁሉ በሚያዩት የምህንድስና ውጤት ይደሰቱ ይደነቁና መልካም ትዝታ ይኖራቸው ዘንድ ዘመናዊ ድልድይ መገንባቱ ተገቢ ነው፡፡
- የባህርዳር ከተማን ውበት በመጨመር ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ የአይን ማረፊያ ሊሆኑ ከሚችሉ መሰረተ ልማቶች አንፃር ይህ ዘመናዊ ድልድይ የሚገነባበት ስፍራ እጅግ ተመራጭ ከመሆኑም ባሻገር በተለይም የድልድዩን አይነትና ዲዛይን በመምረጥ ሂደት ውስጥ በነበረው ትግል በባህርዳር ቤተመንግስት ተራራ ላይ በተደጋጋሚ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ከተማዋን ከዳር እስከዳር በመቃኘት ከጣና ሀይቅ ውበት፣ ከዩንቨርሰቲውና ከስታዲየሙ ውበት ከሰማእታት ሀውልትና ከአባይ ማዶ ውበት በተጨማሪ ከተማዋ አንድ ትልቅ ነገር እንደጎደላት በባለሙያዎች ምናባዊ እይታ ውስጥ ለመቅረፅ የተደረገው ሙከራ ታላቅ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ይህም በተመረጠው ስፍራ ላይ አሁን ሊገነባ ያለውን አይነት ድልድይ ቢገነባ የከተማዋን ውበት ሙሉ ከማድረግም ባለፈ በተለይ ይህ ዘመናዊ ድልድይ ዛሬ በልዩ ልዩ የአለም

ሀገሮች በፊልምና በቦታው ተገኝቶ ማየት እንደሚቻለው የባለኬብል ተንጠልጣይ ድልድዮች ስትራክቸርና ገመዶች መሉ በመሉ በልዩ ልዩ የኤሌክትሪክ መብራቶች ስለሚያጌጡ በምሽትም ጭምር የድልድዩን ቅርፅ በማየት የነዋሪውንና የቱሪስትን ደስታ ከመጨመርም ባለፈ ለሆቴሎች ግንባታና ለፊልም ስራ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ጥናቶችና አለምአቀፍ ስብሰባዎች ተመራጭ ከተማ ያደርጋታል፡፡ ይህን ውብት ዛሬ ላይ በምናብ ለማየት ቤተመንግስት ተራራ ላይ መውጣትና ከተማዋን መቃኘት ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

- በባህርዳር ከተማ የሚገኘው ነባሩ የአባይ ወንዝ ድልድይ ከመገንባቱ ከ1950 ዎቹ በፊት በሀገራችን ረጅም ድልድዮችን ዲዛይን የማድረግና የመገንባቱ ሂደት ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ባለሙያዎች የሚከናወን የነበረ ሲሆን ርዝመቱ እስከ 170 ሜትር የሚደርስ ረጅም ድልድይን በታላቁ አባይ ወንዝ ላይ ዲዛይንም ሆነ ግንባታውን ማድረግ በኢትዮጲያውያን አይቻልም የሚለውን አስተሳሰብና ፍራቻ በመስበር ሙሉ በሙሉ በሀገራችን ባለሙያዎች ተሰርቶ በመጠናቀቁ በዘመኑ ከፍተኛ የሀገርና የባለሙያዎች ኩራት የሆነና በቀጣይነትም በባሮ ወንዝ ላይ በጋምቤላ ከተማ ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ ቀጥሎም በነቀምት ቡሬ መንገድ ላይ የሚገኘውን የአባይ ድልድይ ግንባታ በማካሄድ ብቃት እንዳለ ለማስመስከር በር የከፈተና እንደነበር ይታወሳል፡፡ ዛሬ ደግሞ ምንም እንኳ የግንባታ ቴክኖሎጂውና ልምዱ ባይዳብርም ይህ አይነቱን ልዩና ዘመናዊ ድልድይ ለማስገንባት በሚያስችል የዲዛይን ሀሳብ ላይ ከውጭ ባለሙያዎች ጋር እኩል መደራደር የሚያስችል የድልድይ ባለሙያዎቻችን እውቀት ያደገበት ጊዜ ላይ በመድረሳችን ዘመናዊ ድልድይን በወረቀትና በፊልም ከማየት ባለፈ በሀገራችን ለማስገንባት የምንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናልና ይህን ማድረጋችንም ተገቢ ይሆናል፡፡

## 3 ተጨማሪ መረጃ

የአባይ ወንዝን የሚያቋርጡ የአስሩ ድልድዮች አጭር መረጃ የሚከተለውን ይመስላል

| It. No. | Bridge Name | ConstructionYear | Bridge Length, mt | Route Location | Bridge Type | Constructed by |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Abay No.1 | 1618 | 32 | 42 km down stream from Tana Lake | Masonry Arch | Portuguese |
| 2* | Abay No.2 | 1660 | 40 | Motta DebreTabor | Masonry Arch | Portuguese |
| 3 | Abay No.3 | 1947 | 213 | Gohatsion Dejen | RC Arch+ RCDG | Italy |
| 4 | Abay No.4 | 1959 | 169 | Merawi Bahrdar | RCDG | IHA / Ethiopia |
| 5 | Abay No. 5 | 1990 | 235 | Bure Nekempt | PC Box Girder | Blue Nile PLC, /Ethiopia |
| 6 | Abay No.6 | 2008 Altern. Of No 3 | 303 | Gohatsion Dejen | Extradosed ( Cable+RC Box) | Kajima Corp, Japan |
| 7 | Abay No.7 | 2010 | 320 | Assosa Guba | Stell truss + RCDG | Syno Hydro, China |
| 8 | Abay No.8 | 2014 | 280 | Combolcha Gundewoyn | PC Box Girder | CGCOC, China |
| 9 | Abay No.9 | Under construction Repl of No.2 | 220 | Motta - DebreTabor | PC Box Girder | Zhongmei- JTE / China |
| 10 | Abay No.10 | @ Commencement stage | 380 | BahirDar Town | Extradosed | CCCC / China |

*ግርማ ወርቁ ( ኢ.ር)*
*የድልድይ ሀብት አስተዳደር ቡድን መሪ (ኢ.መባ)*
*ሚያዝያ 2010 ዓም*